***መድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ – ለተባበረ፤ ጠንካራ፤ ውጤታማ የመድብለ ባህላዊ አውስትራሊያን ለመፍጠር የመንግሥት ህዝባዊ ጽሁፍ መግለጫ ሲሆን፤ ለሚቀጥሉት ዓመታት ቅድሚያ ለሚሰጣቸውና የአሰራር መመሪያዎችን ያወጣል።***

## *መግቢያ*

### የአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስተር

በዓለም ውስጥ ካሉት የመድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ አውስትራሊያ በጣም ጥሩ ውጤት አላት።

እኛ እንደ አውስትራሊያ የመጀመሪያው ተወላጆች የጥንት ስንሆን፤ በምድር ላይ ጥንታዊ እና ቀጣይ የሆነ ሰብአዊ ባህል ያለን ከ 50,000 ዓመታት በላይ ይህችን አገር ስንከባከብ እንደነበር ነው።

ከዓለም ማንኛውም አገር፤ እምነት፤ ጎሳ ለመጡ ማይግራንት/ስደተኛ ተቀባይ እናት አገር እንደመሆኗ መጠን እኛ እንደ ልጅ ገና አዳጊ ነን።

አውስትራሊያ የኢሚግሬሽን ሃገር ናት። አሁን ያለው ህዝብ ግማሹ በውጭ አገር የተወለደ ወይም ቢያንስ አንደኛው ወላጅ በውጭ አገር የተወለደ ነው።

እንዲሁም እኛ ከተለያየ ባህል፤ ጎሳ፤ እምነት ተከታይና ሃገር የመጣን ነን።

እኛነታችን የሚገለጸው ከመጣንበት ጎሳ፣ ሃይማኖት ወይም ባህል መሰረት ሳይሆን፤ ነገር ግን ነጻነትን፤ ዲሞክራሲን፤ ህግን በመከተልና የእኩልነት እድልን– “ለሁሉም እኩል አገባብን” ዋጋ በመስጠት አብሮ በመሳተፍ ይሆናል።

ሁላችንን የሚያስተሳስረን በጋራ መከባበር– እያንዳንዳችን በእኩልነት መከባበር፤ ተመሳሳይ አክብሮት፤ ተመሳሳይ እድሎችን እንድናገኝ ከፍተኛ የእውቅና ድጋፍ ይሰጣል።

እንዲሁም ለሃገር ደህንነት - ለሃገራችን፤ ለህዝባችንና ለእኛ ማንነት ዋጋ ለመከላከል በምናደርገው የቁርጠኝነት ውሳኔ ነጻነታችን የተመሰረተው እና የጸናው በዚህ መሠረት ነው፤በዓለም አቀፍ ፍርሃትና አስተማማኝ ባልሆነበት ጊዜ፤ አውስትራሊያ ስምምነት፤ እኩልነት፡ የእድገት አገር፡ እና ልዩነትን በአንድነት የምታቅፍ አገር በመሆን ቋሚ ምሳሌ ናት።

*በመድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ  የእኛ ጽሁፋዊ መግለጫ: በተባበረ፤ ጠንካራ፤ ውጤታማ* እና መንግሥት ለመድብለ ባህላዊ አውስትራሊያውን መስዋእትነት ማደስ እና ማጠናከር፤ ይህም ለዘረኝነትና አድልዎ ለመፍጠር ቦታ እንደሌለው ነው።

*በመድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ  የእኛ ጽሁፋዊ መግለጫ: የተባበረ፤ ጠንካራ፤ ውጤታማ ለሁሉም አውስትራሊያውያን ከምስጋና  ጋር አቀርባለሁ።*



**The Hon Malcolm Turnbull MP**
የአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስተር

# ከማሕበራዊ አገልግሎቶች ሚኒስተር እና ከማሕበራዊ አገልግሎቶች ምክትል ሚኒስተር እንዲሁም ከመድብለ ባህላዊ ጉዳይ በጣምራ የተላለፈ መልእክት

ባለን ጠንካራና ውጤታማ መድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ ሁሉም አውስትራሊያዊ መኩራት ይችላል። የአውስትራሊያ ታሪክ የጀመረው ራቅ ካለው እና ካለፈው ዘመን በአውስትራሊያውያን አቦርጅናል እና ቶረስ ስትራት አይላንደርስ ሲሆን በጊዜው ከተመሠረቱት የእንግሊዝ ተቋማት ጋራ አብሮ በማደግ ከዚያም ከሩቅ እና ከሰፊ ቦታ በመጡ ሰዎች እድገቱ ቀጥሏል፤

እኛ የምንደሰትበት ነጻነትና ደህንነት ድንገተኛ አይደለም፤ በተከታታይ የነበሩት መንግሥታት ልዩነትን በአንድነት የሚያቅፍ እና ልዩ የሆነ ብሔራዊ መለያችን ላይ በማተኮር እና የመዋሀድ እና የሕዝብ አንድነትን ጠቀሜታ የሚያሳይ ራእይ ለሕብረተሰባችን በማዘጋጀታቸው ነው። የሽብርተኝነት እና አክራሪነት መስፋፋት በብዙ ሰዎች ላይ ፍርሃት እየጨመረ በሄደበት ዘመን ለዲሞክራሲ ለእድል እና ለጋራ እሴቶች ያለንን ጽኑ መስዋእትነት ለማጠናከር ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም። ለሃገራችን ደህንነትና ለህዝባችን ነጻነት የአውስትራሊያ መንግሥት ያረጋግጣል። በእኛ *መድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ ጽሁፋዊ መግለጫ: የተባበረ፣ ጠንካራ፣ ውጤታማ፣ መንግሥት* ባለፈው ጊዜ ያገኘነውን ጥሩ ውጤትና ለወደፊት ብልጽግና ሊረዱን የሚችሉትን እሴቶች ለይቶ አስቀምጧል፤ ።

ይህ መግለጫ የባህላዊ ውህደት ካሉን ከፍተኛ ጥንካሬዎች ውስጥ አንደኛው እንደሆነ ያሳውቃል። ይህም ሁሉን የሚያካትት እና መልካም ኑሮን ለመኖር እድል የሚሰጥ ነገርን ለመገንባት የሚረዳን ነው። ይህ ያለንን የዲሞክራሲ ተቋም እና የህግ የበላይነት ማእከል በማድረግ ሲሆን አውስትራሊያኖችን ሁላችንም የማክበር ሃላፊነት እንዳለብን ጽሁፉ ግልጽ ያደርጋል።

የእኛን መድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ በበለጠ ለማጠናከር ይህ ጽሁፍ መግለጫ መሰረታዊ እንደሆነና ያለውን ነጻነትና የወደፊት ጥሩ አጋጣሚን ያለምንም መዳከም ለመቀጠል ከሁሉም አውስትራሊያዊ ጋር አብሮ ለመሥራት ፍላጎታችን ነው።



**The Hon Christian Porter MP**
የማሕበራዊ አገልግሎት ሚኒስተር



**Senator The Hon Zed Seselja**
ረዳት ሚኒስተር የማሕበራዊ አገልግሎት  እና የመድብለ ባህላዊ ጉዳይ

## *መድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ: የተባበረ፤ ጠንካራ፤ ውጤታማ*

**የእኛን ታሪክ ማካፈል**

በዓለም ውስጥ አውስትራሊያ በጣም ውጤታማ የሆነ የመድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ ያላት ይህም የብዙ ባህሎች፤ ልምዶች፤ እምነቶች እና ወግ ልምዶች የተባበረባት አገር ናት። እንደ ሃገር መጠን ከ 300 በላይ የተለያዩ ትውልዶችን በማሳተፍ የሚገባንን ፈጽመናል — ከመጀመሪያ የአውስትራሊያ ተወላጅ እስከ አሁን የደረሰበት ትውልድ አድርሰናል።

የጋራ እሴቶቻችን እና ለነጻነት፤ ደህንነት እና ለእድገት መስዋእትነት መሠረት ላደረገው መድብለ ባህል ምስጋና ይግባውና ከፊሉን አሳምረነዋል።

ሃገራችን በአቦርጂናልና በቶረስ ስትራት አይላንደርስ ህዝብ የተሞላች ስትሆን ይህም በፕላኔት ላይ የድሮ የቆየ ባህል የሚኖርባትና በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝቦች አዲስ ህይወትን ለመመስረት የመረጧት አገር ናት።

የመጀመሪያ አውስትራሊያኖች ከ50,000 ዓመታት በላይ አሁን አውስትራሊያ ብለን በምንጠራት መሬት ላይ እንደኖሩ፤ እንደተማሩና እንደተላመዱም ነው። ጎን ለጎን በመኖር ከ250 በላይ የቋንቋ ቡድኖች ወይም 'አገራት' በመላው አህጉር ውስጥ እንዳላቸው፤ ይህም እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ባህል፤ እምነትና ቋንቋ አለው። ከነዚህ አገራት የተወለዱት በፕላኔት ላይ ላለው የድሮ ባህል እንዲቆይ የሚወክሉ ሲሆን እንዲሁም ማንኛውም ሌላ ሰዎች ማስታወስ ከሚችሉት በላይ የጊዜና ቦታዎች ታሪኮች አሏቸው።

ዘመናዊ አውስትራሊያን ከብሪቴንና ከአይሪሽ ሰፈራ ምስረታ ጋር ታሪኩ እንደቀጠለና ከዚያም የእኛ ፓርላመንታሪ ዲሞክራሲ፤ ተቋማት፤ እና ህግ በመመስረት ታሪኩ ቀጥሏል። ከመላው አህጉራት በመጣና አውስትራሊያን እንደቤቱ ላደረገ በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብን ያካተተ ታሪካችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዳደገ ነው።

ዛሬ ወደዚህ አገር ለገቡ ሰዎች በእኛ ነጻና ግልጽ በሆነ ሕብረተሰብ ውስጥ ተሳታፊ አካል እንዲሆኑ አውስትራሊያ እምታጋብዘው ህይወታቸውን እንዲመሰርቱና ለእኛ አገር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ነው።

ከጊዜ ብዛት ብዙ ሰዎች ሲሰባሰቡ የእኛን መዋቅር መገንባት ፤ ማህበረሰባችንን ማድመቅ፤ ያለንን ባህላዊ ልምዶች ማዳበር፤ የእኛን እድሎች እንደሚጨምርና በተለይም ከዓለም ጋር ያለንን ግንኙነትና የአመለካከት ዘይቤ ለማዳበር በጣም ጠቃሚ ነው።

በመንግሥት፤ ማህበረሰብ እና ግለሰቦች መካከል – በሃገራዊነት ሳይለይ– የጋራ ግዴታዎችን ማዳበር፤ የመቋቋም እና የአባልነት ስሜትን ያጠናክራል።
በጋራ ባለን እሴቶች ፤ መብቶችና ሃላፊነቶች የዛሬዋን ዘመናዊ እና ሀብታም አውስትራሊያን ገንብተናል።

**ግምትን ማካፈል የጋራ እሴቶች**

የእኛ እሴቶች ዋጋ ወደ አንድነት እንደሚያመጣንና በመካከላችን ማሕበራዊ ግንኙነትን ይፈጥርልናል። ይህ ለሕብረተሰባችን መሠረት እና ሁሉን የሚያሳትፍ የተጋራ ወደፊት ያቀርብልናል። የእኛ እሴቶች መሰረት:

*ማክበር*

የአውስትራሊያን ህግ እና ደንብ እናከብራለን ብሎም ሃላፊነት አለብን፤።

የሁሉንም ግለሰቦች መብትና ክብር እናከብራለን።

ለእኛ ብዙሃነትና የጋራ መከባበር መኖር ማለት በተገቢ እና ርህራሄ በተሞላበት ማስተናገድን ያካትታል።

***እኩልነት***

የወንዶችንና ሴቶችን እኩልነት እንደግፋለን።

በህግ ፊት እኩልነትን እናምናለን።

ለሁሉም የእኩልነት እድል እንዲያገኝ እናምናለን።

*ነጻነት*

ለነጻነት ያለን መስዋእትነት መሰረታዊ ነው።

የአስተሳሰብ፤ የንግግር፤ የሃይማኖት፤ መሪነትን ወስዶ በሃላፊነት መስራት እና ማህበር የማደራጀት ነጻነትን እንደግፋለን።

የፓርላመንታሪ ዲሞክራሲ እንፈጽማለን።

የእኛን ሲቪል ተግባራት ለማስፈጸም ሃላፊነት እንወስዳለን።

የእኛን ግምት ዋጋ አሳንሶ በመናቅ የሚደረግ ተግባራትና ባህሪያት በአውስትራሊያ ውስጥ ቦታ የላቸውም።

በሃገራችን የኢኮኖሚ ውጤታማ፤ የባህልና ሃይማኖት ነጻነት እና ስብጥርነት ሁላችንም እንጠቀማለን። ለአውስትራሊያ ህዝብ ፍላጎት በጥሩ ሁኔታ እንዲሳካ ተደርጎ ለመያዝ ላለን የጋራ እሴት ከባድ መስዋእትነትን አብሮ መያዝ አለበት።

**መብቶችንና ሃላፊነቶችን ማካፈል**

በጋራ መከባበርና የጋር ሃላፊነት ጠቃሚ ስለመሆኑ እናውቃለን። እንደ መድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ መሆን እኛ ውጤታማ የምንሆነው መብቶችንና ሃላፊነትን በማመዛዘን የተረጋጋ፤ በፍጥነት የሚያገግም እና የተጣጣመ ሕብረተሰብ እንዲሆን በማረጋገጥ፤ በእኛ ሀብት ላይ ጥቅም እንዲያገኙ — ለሁሉም ሰው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ እድሉን መስጠት እንፈልጋለን

የእኛ ሕብረተሰብ የተመሠረተው በሊብራል-ዲሞክራሲያዊ ባህል መሰረት ነው፤ በዚህም የእያንዳንዱ ግለሰብ መሰረታዊ መብቶች የማይጣሱ ናቸው።

ዜግነት ልዩ መብት ነው፡ በአውስትራሊያ የዜግነት ምረቃ ስነ-ስርዓት ላይ፤ አዲስ ዜጎች ቃል ኪዳን ያደርጋሉ ይህውም "የዲሞክራሲያዊ እምነት የምካፈለው፤ መብትና ነጻነት እማከብረው፤ ሕጉን የማከብረው እና የምታዘዘው *ለአውስትራሊያና ለህዝቧ ታማኝ ለመሆን፤ ቃል በመግባት አረጋግጣለሁ"።*
በእኛ ሃገር ያለ ማንኛውም ሰው የአውስትራሊያ ዜጋ ቢሆንም ባይሆንም የአውስትራሊያን ህጎች መከተል፤ የእኛን ዲሞክራሲያዊ አሰራር መደገፍ፤ እና ሁሉንም ሰው በአክብሮት ማስተናገድ እንዳለባቸው ይጠበቃል።

**ደህንነቱ የተጠበቀ አውስትራሊያ**

የተለያየ ስብጥር  ያለውና ሰላማዊ አውስትራሊያን ማጠናከር የሃገራችን ደህንነት ይሆናል። የአውስትራሊያ መንግሥት ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ለሁሉም አውስትራሊያዊ ደህንነት ይሆናል። በዓለም ዙሪያ በቅርቡ ለተፈጠረው የሽብርተኛ ጥቃት በአውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ ግልጽ የሆነ አሳሳቢ ጉዳይ ፈጥሯል።

ለዚህ ዛቻ መንግሥት የሰጠው ምላሽ በሽበርተኝነት ዙሪያ ላይ ማጣራት፤ ጠንካራ ድንበሮችንና ጠንካራ የደህንነት ጥበቃ በቀጣይነት ማካሄድ እንደሆነ ነው። ይህ የሚረዳው፤ በአውስትራሊያ ግልጽ፤ ሁሉን ያካተተ፤ ነጻና ደህነት ያለው ሕብረተሰብ እንዲኖራት ለማረጋገጥ ነው።

ነገር ግን በዚህ ዛቻ  ምክንያት፤ በእኛ የጋራ እሴቶች እና ሃገራዊ አንድነት ላይ አንደራደርም። መንግሥት በአውስትራሊያ ማህበረሰብ ደህንነት እንዲኖር የሚያበረታታው አንድ በሚያደርጉን ነገሮች እና ልዩነታችንን በጋራ መከባበር ላይ በማተኮር ነው።

**ለወደፊት ያለን ራዕይ ማካፈል**

የአውስትራሊያ አንድነት የመጣው ለሃገራችን በምንጋራው መስዋእትነት ዲሞክራሲያዊ ተቋማትና እሴት ነው። ሁላችንም ተቀባይነትንና መረዳትን ማበረታታት የእኛ ሕብረተስብ ደህንነት ቀጣይ እንዲሆን፤ ሁሉን ያቀፈ እና ሰላማዊ ህበረተሰብ እንዲሆን ማበረታታት አለብን።
በዚህ ጽሁፋዊ መግለጫ ውስጥ መንግሥት ስለ የጋርዮሽ መከባበር ስርአትንና የጎሳ ጥላቻንና አድልዎ መፍጠር በአውስትራሊያ ሕብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነት ስለሌለው ለማስወገድ በተከታታይ ያሳስባል።

የሌላ መንግሥት ፖሊሲዎችና መርሃግብሮችን ያካተተ ሲሆን፤ ይህም ከብዙ የተለያዩ ማህበረሰብና በፈቃደኝነት እንቅስቃሴዎች፤ ማነቃቂያ፤ ድጋፍ እና ያለንን አንድነት መቀጠል። ለምሳሌ:

- የጐልማሳ ማይግራንት/መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም ድጋፍ የሚፈቀድላቸው ማይግራንት/ስደተኞች እና በስብአዊነት ለገቡ መሰረታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመማርና በአውስትራሊያዊ ሕብረተሰብ ውስጥ በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሳተፍ እንዲችሉ የሰፈራ ችሎታ ትምህርት ይቀርብላቸዋል።

- የመንግሥት መድብለ ባህላዊ መገልገያ እና የትክክለኛ ፍትህ ፖሊሲ ማረጋገጫ መርሃ ግብር እና አገልግሎቶች በኩል ከየትም ባህልና ቋንቋ የሚነገርበት አገር ለመጡ አውስትራሊያውያን በሙሉ ያላቸውን ፍላጎት ያሟላል።

- ለአዲስ ማይግራንት/መጤዎች በሲቪክ ሕብረተሰብ ውስጥ ሙሉ የእንቅስቃሴ ተሳትፎ በማካሄድ ወደ ዜግነት የመሸጋገሪያ መንገድ እድሉ ይፈጥርላቸዋል።

- መንግሥት ጠንከር ያለና በተለያየ መድብለ ባህላዊ የብዙሀን መገናኛ በራዲዮ፣ ህትመት፤ በመስመር እና በተለቪዥን ላይ ድጋፍ ያደርጋል።

- የውህደት ቀን/Harmony Day የተመሰረተው በ1999 ዓ.ም ውስጥ እንደሆነና አሁን በየዓመቱ በሺዎች በሚቆጠሩ አውስትራሊያውያን እንደሚከበር ይህም በጣምራ መሆንን፤ መከባበርን እና በዓሉ የሁሉም እንደሆነ መልእክት ያስተላልፋል።

- የአውስትራሊያ መድብለ ባህላዊ መማክርት/Australian Multicultural Council እንደ ዋና ቁልፍ ተወካይ አካል እንደሆነ ለመንግሥት መልእክት አስተላላፊና በማንም ተጽእኖ የሌለው አማካሪ ነው።

የእኛን ውህደትና ብልጽግና አውስትራሊያውያን በማቅለል አይቀበሉትም። አብሮ በጋራ —እንደ ግለሰቦች፤ ቡድኖች እና በሁሉም የመንግሥት ደረጃዎች ያሉት— በምንሰጠው ምክር ዋጋ እና በአሰራር መመሪያ በመከተል ጠንካራ የሆነ፤ በበለጠ የተሳሰረና የበለጸገ ማህበረሰባትን ለማነጽ እንቀጥላለን።

## በቅርቡ ለገቡ በኢኮኖሚና ማሕበራዊ ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ስለማበረታታት

አውስትራሊያ በማይግራንት/መጤዎች አስተዋጽኦ በኩል ለእኛ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ከፍተኛ ታሪክ አላት። ይህ ከእኛ ሁሉን ካካተተ መድብለ ባህላዊ ሕብረተሰብ ጋር ለውጤታማ ሃገራችን በአዲስ ማይግራንትስ/መጤዎች አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ እድሉን ማቅረቡ ዛሬም ይቀጥላል።

በማህበረሰባት፤ በትምህርት ቤቶች፤ አትራፊ ባልሆኑ ድርጅቶች፤ ለእምነት- በተመሰረቱ ድርጅቶች፤ በቀጣሪዎች እና በመንግሥታት የጋራ ጥረት ለአውስትራሊያ የሕብረተሰብ ህዝብ አወንታዊ አስተዋጽኦ የማቅረብ እድሎችን ያቀርባል።

ወደ አውስትራሊያ የተሰደዱ ሰዎች ለተሻለ ህይወት ወይም አዲስ እድሎችን ስለማፈላለግ ያላቸውን ሃሳብ ያካፍላሉ።

በተመሳሳይ ጊዜ፤ በአዲስ ማይግራንት/መጤዎችና ቤተሰቦቻቸው ከኢኮኖሚና ማሕበራዊ ጋር መዋሃዱ ለወደፊት ጠቃሚ ይሆናል። ከአዲስ መኖሪያ ሃገራቸው ጋር እንደተገናኙ ይሰማቸውና በአውስትራሊያ ሕብረተሰብ አካል የመሆን ስሜት ሊፈጥርላቸው ይችላል።

አዲስ ማይግራንት/መጤዎች በአውስትራሊያ ህይወት ኑሮ እንቅስቃሴ ላይ በጥሩ እንዲዋሃዱ ተብሎ ለታቀደ የሰፈራ አሰራር መዋቅር መንግሥት ያቀርባል። የማይግራንት/መጤዎች እራሳቸውን እንዲችሉና በአውስትራሊያ ማህበረሰብ ተሳታፊ አባላት እንዲሆኑ የሰፈራ መርሃ ግብር ያግዛል።

አንዳንድ አዲስ መጤዎች፤ በተለይ በስደተኛ እና በስብአዊ ፕሮግራም ወደ አውስትራሊያ ለገቡ ለየት ያለ ድጋፍ ጥቅም ያገኛሉ። በዚህ የሚካተት የእንግሊዝኛ ትምህርት እርዳታና ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ወይም የሥራ መቀጠር ችሎታን ማግኘት ይሆናል። በተለይ በሰብአዊነት ለገቡ ለመጀመሪያ አምስት ዓመታት አውስትራሊያ ቆይታቸው መንግሥት ለመርዳት እያረጋገጠ፤ ስለዚህም የተሻለ ህይወት ማነጽ እንደሚችሉና ለሕብረተሰቡ አባላት ብቃት ያለው አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ነው። በስብአዊነት ለገቡ ስደተኞች የሚሆን ለተሻሻለ እንግሊዝኛ ቋንቋ፤ ትምህርትና የሥራ መቀጠር ጥሩ ውጤት ለማስገኘት፤ በአሁን ጊዜ የአውስትራሊያ መንግሥት ለሰፈራ አገልግሎቶችን በማሻሻል እቅድ አውጥቷል።

## ያለንን የተዋሃደ ብዙህነት እና ሃገራዊ ፍላጎት ጥቅም አብሮ በጋራ ስለማቀናጀት

እንግሊዝኛ የሃገራችን ብሄራዊ ቋንቋ ሆኖ ይቆያል፤ እና ይህም ለማይግራንት/መጤ ውህደት ዋናው መሳሪያ ይሆናል። በተመሳሳይ ጊዜ፤ ያለን የመድብለ ቋንቋ ሥራ መዋቅር ለንግድ ሥራ አድማሳት እንደሚያሰፋውና በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ የአውስትራሊያን ውድድር እንዲጨምር ያደርጋል።
የእኛ ባህላዊ ውህደት ካሉን ሃብት ንብረቶች አንዱ ሲሆን– አዲስ ግኝትን፤ ፈጠራንና ከፍተኛ ጥንካሬነትን ያበረታታል። የእኛ ኢኮኖሚ የሚያድገው ባለን የሰራተኞች ውህደት ችሎታ፤ እውቀት፤ የቋንቋ ብቃት፤ ግንኙነት አውታርና ፈጠራ አስተዋጽኦ ይሆናል። የእኛ ውጤታማና ተወዳዳሪ መሆን በዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ በኩል ያለንን ግንኙነት እውቅና እና እድል ለማግኘት ያለንን ችሎታ ያጠናክራል።

በዚህ የሚካተት ብዙዎች ጊዜያዊ ማይግራንት/መጤዎች እዚህ በሚኖሩበት ወቅት ለአውስትራሊያ ኢኮኖሚና ሕብረተሰብ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ብዙዎቹ በቋሚነት አውስትራሊያ ውስጥ ሲሰፍሩ፤ ሌሎቹ ደግሞ ወደ አገራቸው ወይም ሌላ አገር ቢሄዱም፤ በውጭ አገር ያለንን ባህላዊ፤ ንግድና ኢኮኖሚ እድሎች በበለጠ ያጠናክራል።

መንግሥት፤ የንግድ ተቋማትና ኢንዱስትሪ ሁሉም የእኛን የብዙ ውህደት ሰራተኞች ጥቅም በማበረታታት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

## የበለጸገ እና ማሕበራዊ አንድነት ያለውን ማህበረሰባት ለማነጽ ስለመቀጠሉ

በጋራ የምንጋራቸው የአውስትራሊያ እሴቶች ለኢኮኖሚያችን ብልጽግና ብሎም ሁሉን አቀፍ ለሆነ ማህበራዊ ህብረተሰብ የማእዘን ድንጋይ ናቸው።

ያለንን ባህላዊ ቅርስ ማካፈሉ፤ አውስትራሊያዊ ማለት ምን እንደሆነ በሚደረግ ክብረ በአል ውስጥ አንድ አካል ሲሆን፤ ይህም ባለን ሕብረተሰብ ውስጥ እያንዳንዱ ስለመካተቱ ስሜት እንዲያድርበት ይረዳል። የማህበረሰብ መግባባት ሃገራዊ አንድነትን ይፈጥራል። ያጋራ ልምድ የጋርዮሽ ታሪክን ይፈጥራል፤ ብሎም የወደፊቱን ጋርዮሽ ይቀርጻል።

በተቃራኒ ደግሞ ዘረኝነት እና አድልዎ ፈጠራ ሕብረተሰባችንን ያዳክማል። የዘር ጥላቻን የሚገፋፉ ሰዎች እናወግዛለን።

የተለያየ እምነት ባላቸው እና የተለያየ ባህል ባላቸው መሀከል የሚደረግ መደበኛ ውይይት ማካሄዱ በማህበረሰባት ውስጥ ሊከሰት የሚችልን ችግር በመቀነስ እና አንድነትንና መተባበርን ይፈጥራል። እንደዚህ ዓይነቱ ውይይት ያለውን የጥላቻ ግምት በመቀነስ፤ በተለያዩ ባህሎች መካከል መረዳዳት እንዲዳብር፤ በተለያዩ ጐሳዎችና የሃይማኖት ቡድኖች እንዲሁም የማንነት ስሜትና እምነትን ያዳብራል።

የመጣበት ባህል፤ ትውልድ ስፍራና ሃይማኖት ሳይወስነው በአውስትራሊያ ውስጥ ያለ ወይም ወደ አውስትራሊያ የመጣ ማንኛውም ሰው ከእያንዳንዱ ሰው ጋር ለመግባባት እና ለመረዳት መጣር ሃላፊነት እንዳለበትና ማንኛውንም ዓይነት ዘረኝነት እና አክራሪነትን ማስወገድ አለበት።

### ማጠቃለያ

ቀጣዩ የአውስትራሊያ መንግሥታት ለመድብለ ባህላዊ አውስትራሊያ እንዲመሰረት ጠንካራ የሆነ ሃሳብ አላቸው። በተከታታይ ስልጣን ላይ የወጡት የአውስትራሊያ መንግሥታት ለአውስትራሊያ መድብለ ባህል እንዲሳካ ጽኑ መሰረት ጥለዋል፤ በዚህ አዲስ ጽሁፋዊ መግለጫ መንግሥት የጀመረውን ጥረት በየጊዜው ማደስና ማጠናከር: ሕብረተሰባችንን ለሚያጠናክር ባለን እሴቶች እና ሃላፊነቶች በዚህ መልእክት ላይ በግልጽ እንደቀረበ፤ ይህም ለብሔራዊ ፍላጎት ድጋፍ እና እንዴት ችግሮችን እንደምንወጣ መመሪያ ያቀርባል። ይህ ራዕይ የሚያቀርበው ለወደፊት ጠንካራና ውጤታማ የሆነ መድብለ ባህላዊ ሃገር በመፍጠር፤ ለአውስትራሊያ ነጻነትና ብልጽግና በእኛ ታማኝነት አንድነትን ለመፍጠር ነው።